## ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት ምለሳ በጣም አስፈላጊ ነገሮች

(ቅዳሜ—የምሽት ክፍለ ጊዜ)

መልእክት ስድስት

## በሕይወት ለማደጋችንና በአገልግሎት ጠቃሚ ለመሆናችን ተፈጥሮአዊ ባህሪያችንን ማደብ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ማቴ. 16፡22-26፤ ገላ. 2፡20፤
2 ቆሮ. 1፡8-9፤ 2፡15፤ 3፡3-6፤ 4፡5፤ 5፡20፤ ኤፌ. 6፡20

### I. በሕይወት ለማደጋችን እና በአገልግሎት ጠቃሚ ለመሆናችን ተፈጥሮአዊ ባህሪያችንን ማደብ አለብን፡-

ሀ. ተፈጥሮአዊ ባህሪያችን በውልደታችን ባለን ቅንብር የሆንነውን ነገር ያመለክታል፣ ጠባያችን ደግሞ የተፈጥሮአዊ ባህሪያችን ውጫዊ መገለጥ ነው፤ ተፈጥሮአዊ ባህሪ በውስጥ የሆንነው ነገር ነው፣ ጠባይ ደግሞ በውጭ የምንገልጠው ነው።

ለ. ውስጣዊው ተፈጥሮአዊ ባህሪ እና ውጫዊው ጠባይ የማንነታችን ንጥር እና ይዘት ናቸው፤ በውስጣችን ያለው እኔነት ተፈጥሮአዊው ባህሪያችን ሲሆን የሚገለጠው እኔነት ደግሞ ጠባያችን ነው።

ሐ. በክርስቲያን ሕይወት እና በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ጠቃሚነታችንን በእጅጉ የሚያጠፋው ነገር በተፈጥሮአዊው ባህሪያችን መሠረት መኖራችን ነው፤ ይህ በመለኮታዊው ሕይወት የማደጋችን እውነተኛ ጠላት እና በጌታ እጅ ያለንን ጠቃሚነት የሚያበላሽ ዋና ምክንያት ነው።

መ. በቅንብራችን፣ በተፈጥሮአዊው ባህሪያችን ውስጥ ያለውን "እባጭ" ማስወገድ መማር አለብን፤ ይህንን "እባጭ" ካስወገድነው በሕይወት እድገታችን ያለምንም እንቅፋት በፍጥነት እናድጋለን፣ በተጨማሪም ለጌታ የበለጠ ጠቃሚዎች እንሆናለን።

ሠ. ባህሪ በማቴዎስ 16፡23-26 ጥቅም ላይ በዋሉት ቃላቶች ተመላክቷል—*ሃሳብ*፤ *ራሱ*፤ *የነፍስ-ሕይወት*፤ ተፈጥሮአዊ ባህሪ እነዚህን ሁሉ መሠረታዊ ነገሮች ያካትታል፤ በእውነቱ ተፈጥሮአዊው ባህሪያችን እኔነታችን ነው ማለት እንችላለን።

ረ. ተፈጥሮአዊ ባህሪያችንን ማስወገድ ማለት እኛነታችንን እና የነፍስ ሕይወታችንን (ቁ. 22-26)፣ አሮጌው ሰዋችንን (ሮሜ 6፡6) እና "እኔ"ን (ገላ. 2፡20) ማስወገድ ማለት ነው፤ ለጌታ ምን ያህል ጠቃሚ እንደምትሆኑ ወይም ለቤተ ክርስቲያን ምን ያህል ችግር እንደምትፈጥሩ የሚመረኮዘው ተፈጥሮአዊው ባህሪያችሁ በተገደለበት መጠን ላይ ነው፤ ተፈጥሮአዊ ባህሪያችንን ማስወገጃው መንገድ የተሰቀልን ሰዎች መሆናችንን መገንዘብና ማስታወስ እና ቀኑን ሙሉ በዚያ ግንዛቤና እውነታ ውስጥ መቆየት ነው (ቁ. 20፤ 5፡24-25፤ ሮሜ 6፡6፤ 8፡13)።

ሰ. ተፈጥሮአዊው ባህሪያችን እኔነታችን ነው፤ ይህ በእኛ ውስጥ ያለ እና እኛን ነው፤ ተግባራዊ በሆነ መልኩ ለመናገር፣ እኔነትን መካድ ተፈጥሮአዊ ባህሪያችንን መካድ ነው፤ እንደ ክርስቲያኖች ራሳችንን ለመተው እና በሌላ ሕይወት፣ በሕይወት ዛፍ በተመለከተው በተሰቀለው እና ከሞት-በተነሣው ክርስቶስ ለመኖር ባለማቋረጥ መንፈሳችንን በማንቀሳቀስ ክርስቶስን መኖር አለብን—ዘፍ. 2፡9፤ ፊልጵ. 1፡21፤ ራእ. 2፡7፤ 1 ጴጥ. 2፡24፤ 1 ጢሞ. 4፡7-8።

### II. በጌታ ሥራ ውስጥ በተፈጥሮአዊው ባህሪያችን መወሰን የለብንም፤ ይልቁንም፣ እኔነታችንን ራሳችንን፣ ተፈጥሮአዊ ባህሪያችንን የመተው ሕይወት መኖር አለብን፤ እኛ ያለንና ከእኛ የሚወጣው ነገር ሁሉ ወደ ጌታ አገልግሎት ውስጥ መምጣት አይችልም—ሮሜ 1፡9፤ 7፡6፤ 2 ቆሮ. 3፡3-6፤ 4፡5፡-

ሀ. የአንዳንድ ወንድሞች ተፈጥሮአዊ ባህሪ ጠንካራ በራስ-መተማመንን ያንጸባርቃል፤ ባለማቋረጥ እኔነታቸውን በመተውና ከሞት-በሚያስነሣው ሦስታንድ አምላክ ላይ በመደገፍ በራስ መተማመናቸው መገልበጥ አለበት—1፡8-9።

ለ. ሰው ከእግዚአብሔር ያገኘው አብርሆት ትንሽ ሲሆን፣ እግዚአብሔርን የመታዘዝ ችግር እንደማይኖርበት አብልጦ ያስባል፤ ሰው ከፍ ያሉ የይገባኛል ጥያቄዎች ለማቅረብ ሲፈጥን፣ ምንም አይነት ዋጋ ከፍሎ እንደማያውቅ አብልጦ ያረጋግጣል፤ በቃሎቻቸው ከእግዚአብሔር ጋር ቅርበት እንዳላቸው የሚያስመስሉ ሰዎች ምናልባትም ከእርሱ እጅግ የራቁ ናቸው—ማቴ. 6፡1-6፤ 16-18፤ ሉቃ. 18፡9-14፤ ፊልጵ. 3፡3።

ሐ. የአንዳንድ ወንድሞች ተፈጥሮአዊ ባህሪ ሁኔታዎቹ ሙሉ በሙሉ ፍጹም ወይም በቂ እስካልሆኑ ድረስ ለመሥራት እንቢ የሚል ነው፤ መሥራት ከመቻላችን በፊት የተለየ ከባቢ ሁኔታ የሚፈልገውን ተፈጥሮአዊ ባህሪያችንን መተው አለብን—1 ጴጥ. 4፡1፤ 1 ቆሮ. 9፡23-27።

መ. ለአገልግሎቱ መከናወን ከሁሉም ሁኔታዎች ጋር መስማማት በሚችለው፣ ማንኛውንም አይነት አቀባበል መታገስ በሚችለው፣ ማንኛውንም ከባቢ ሁኔታ መቀበል በሚችለው፣ በማንኛውም አይነት ሁኔታ ውስጥ መሥራት በሚችለው እና ሁሉንም አይነት እድል መጠቀም በሚችለው ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር አብረን መሥራት ያስፈልገናል፤ በሁሉም ነገር እና በሁሉም ስፍራ ክርስቶስን የመለማመድን ምሥጢር መማር አለብን—2 ቆሮ. 6፡1-2፤ ፊልጵ. 4፡5-9፤ 11-13።

ሠ. አንደኛው አይነት ተፈጥሮአዊ ባህሪ "ጀግና" የመሆን ነው፤ እንዲህ አይነቱ [ተፈጥሮአዊ ባህሪ] ሁሉንም ነገር አስደናቂ፣ ፍጹም እና ሙሉ በሆነ መንገድ ማድረግ አለበት፤ ሌላው አይነት ተፈጥሮአዊ ባህሪ ደግሞ "ጀግና-ያልሆነ" ነው፤ ጀግና-ያልሆነው ማንኛውንም ነገር ጥልቅ-ዝርዝር እና ሙሉ በሆነ መንገድ አይሠራም።

ረ. አንዳንድ ኃላፊነት የሚሸከሙ ወንድሞች በተፈጥሮአዊ ባህሪያቸው ውስጥ ከሌሎች ጋር ለመቀናጀትና ለመተባበር የሚከለክላቸው ጠንካራ ንጥረ-ነገር አላቸው፤ ብዙውን ጊዜ እነዚህ በጣም ብቃት ያላቸው ናቸው፣ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥም በቀላሉ ችግር ማነሳሳት ይችላሉ፤ በተፈጥሮአዊ ባህሪያቸው የበላይ የመሆን ዝንባሌ፣ የሚጨቁን መንፈስ፤ የሚነቅፍ ንግግር፣ የሌሎችን ስህተት ፈላጊ እና ይቅር የማይል መንፈስ ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ።

ሰ. ሌሎች ኃላፊነት የሚሸከሙ ወንድሞች ሁሉም ሰው እንዲወዳቸው የሚፈልግ እና ማንንም መበደል የማይፈልግ ተፈጥሮአዊ ባህሪ ሊኖራቸው ይችላል፤ ይህ በጌታ ሥራ ያላቸውን ውጤታማነታቸውን ይገድባል፣ ምክንያቱም ጌታ እውነተኛ እና ግልፅ የተግሳፅ እና የማስጠንቀቂያ ቃል በእነርሱ በኩል ለቅዱሳን ለመናገር ሲፈልግ አያደርጉትም—ተዛ. ቆላ. 1፡27-29፤ 1 ተሰ. 5፡12-13፤ 1 ቆሮ. 10፡5-13፤ ዕብ. 3፡7-19፤ 12፡25፦

1. በተጨማሪም እንዲህ አይነት ባህሪ ያላቸው ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን፣ ለቅዱሳን እና ለሥራው ባላቸው ግድ መሰኘት ተገቢ መረዳትና ተገቢ እይታ የሌላቸው እስኪሆኑ በሚያደርግ መጠን እንኳን ሳይቀር ወደ ቅዱሳን ያላቸውን የተፈጥሮአዊ ፍቅር "ልዩ እሳት" ሊገልጡ ይችላሉ—ዘሌ. 2፡11፤ 10፡1-2፤ ዘኍ. 6፡6-7፤ ፊልጵ. 1፡9፤ 1 ጴጥ. 2፡25፤ 5፡2፤ ዕብ. 13፡17።
2. የናዝራዊ ስዕለት ዋናው ክፍል በተፈጥሮአዊ ፍቅር ከሚመጣ ሙትነት ራሳችንን መለየት ነው (ዘኍ. 6፡6-7)፤ በተጨማሪም እህል ቁርባኑ ማር የሌለው መሆኑ ትርጉሙ በክርስቶስ ውስጥ ተፈጥሮአዊ ፍቅር ወይም ተፈጥሮአዊ መልካምነት እንደሌለ ነው (ዘሌ. 2፡11፤ ማቴ. 12፡46-50፤ ማር. 10፡18)።

ሸ. በመካከላችን የነበረው ማንኛውም አመጽ ምንጩ በአመጹ የተሳተፉት ሰዎች ተፈጥሮአዊ ባህሪ ነበር፤ (ከሰይጣን የሚመጣው) ስፍራ መፈለግ የወደቀው ሰው ሁሉ ተፈጥሮአዊ ባህሪ ቀዳሚው ንጥረ-ነገር ነው፤ የልዩነት ሥሩ እኔነት፣ ተፈጥሮአዊው ባህሪ ነው—ኢሳ. 14፡12-13፤ ዘኍ. 12፡1-2፤ 16፡1-3፤ 1 ሳሙ. 15፡10-12፤ ማቴ. 18፡1-4፤ 20፡20-28፤ ሉቃ. 22፡25-27፤ 2 ቆሮ. 10፡4-5።

ቀ. ሁለተኛ ነገሥት 4፡8-10 ሱናማዊቷ ሴት ኤልሳዕ በዚያ ባለፈ ጊዜ ሁሉ ምግብ በማቅረብ እርሱን የመቀበሏን ዘገባ ይሰጣል፤ አንድም መልእክት አልሰጠም ወይም አንድም ተዓምር አላደረገም፣ ነገር ግን ሴቲቱ ምግቡን የተቀበለበትን መንገድ አይታ "ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰው" እንደሆነ ለየችው፤ ኤልሳዕ ለሌሎች የሰጠው ስሜት ይህ ነበር፣ ስለዚህ "እኛ ሌሎች የምንሰጠው ስሜት ምን አይነት ነው" ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን—ተዛ. 2 ቆሮ. 2፡15፤ 5፡20፤ ኤፌ. 6፡20።

በ. ጌታ የውጪውን ሰውነታችንን ከተፈጥሮአዊው ባህሪያችን ጋር ቢሰብርልን፣ ከዚያ ወዲያ ሌሎችን በምንነካ ጊዜ ሁሉ ጠንካራውን እኔነታችንን አናቀርብላቸውም፤ ይልቁንም፣ ሰዎችን በምንነካ ጊዜ ሁሉ መንፈሳችን [ወደ ሌሎች ውስጥ] ይፈስስ ነበር፤ የተፈጥሮአዊ ማንነታችንን ችግሮች አሸንፎ ማለፍ ለእኛ የማይቻል ነው፣ ጌታ ግን ሊያደርገው ይችላል—ዮሐ. 7፡37-38፤ ሉቃ. 18፡24-27፤ 19፡2።

## III. በተቀመመው መንፈስ ውስጥ ባለው በመስቀሉ የሚገድል ንጥረ-ነገር፣ በመንፈስ ቅጣት፣ በክርስቶስ እንደመንፈስ ማብራት እና በቤተ ክርስቲያን ሕይወት፣ ፍሬ-በማፍራት እና ጠቦቶችን በመመገብ መንፈስ ውጫዊው ሰዎችንን፣ እኔነታችንን፣ ተፈጥሮአዊ ባህሪያችንን ያስወግዳል፦

ሀ. ተፈጥሮአዊ ባህሪያችንን ለማስወገድ፣ እኔነትን መካድ እና የመስቀሉን የመግደል ኃይል መተግበር አለብን፤ በመንፈሳችን ያለው የተቀመመው፣ ሁሉን-ያካተተው መንፈስ ተፈጥሮአዊ ባህሪያችንን ሁሉ መግደል የሚችለውን የክርስቶስን ክቡር ሞት እና የክርስቶስን ሞት ጣፋጭነት እና ፍቱንነት እንደሚያካትት በልምምዳችን ማየትና መገንዘብ ያስፈልገናል—ዘጸ. 30፡23-25፤ ፊልጵ. 1፡19፤ ሮሜ 8፡13፦

1. ክርስቶስ እንደተቀመመው መንፈስ የሚፈውሰን፣ ሕያዋን የሚያደርገን እና በውስጣችን ያሉትን አሉታዊ ነገሮች ሁሉ የሚገድል መድኃኒታችን ነው፤ እንደመድኃኒታችን ስንወስደው "የኢየሱስን መሞት" ወይም የኢየሱስን መገደል እንደሰታለን—2 ቆሮ. 4፡10-11።
2. በመንፈስ ውስጥ የመስቀሉ የሚገድል ንጥረ-ነገር አለ፤ በማለዳ እግዚአብሔርን ወደውስጣችን ለመቀበል ራሳችንን ስንተው፣ ቀኑን ሁሉ የመግደል ሂደት በውስጣችን እየተከናወነ እንደሆነ ስሜቱ ይኖረናል።

ለ. የመንፈስ ቅዱስ ቅጣት ግቡ የተሰበሩ ሰዎች እንድንሆን ነው፤ እግዚአብሔር በእኛ መንገድ ማግኘት ከመቻሉ በፊት በፍጹም አለመቻል እና በፍጹም ረዳት-የለሽነት ስፍራ ውስጥ ሊያስቀምጠን ይገባል፤ የምናልፍባቸው መከራዎች አላማቸው እርሱ እንዲገለጥ እግዚአብሔርን የማወቅን ጥቅም መቀበል እንችል ዘንድ ነው—1፡8-9፤ 12፡9-10፤ ኢሳ. 40፡28-31፤ ሆሴ. 6፡1-3፡-

1. የውጪው ሰው መሰበር የተፈጥሮአዊው ባህሪያችን መሰበር ነው፤ ተፈጥሮአዊው ባህሪያችን መንፈሳችን እንዳይለቀቅ አስቸጋሪ ያደርግብናል፤ በእግዚአብሔር ያልተሰበረ ሰው የጌታ ሥራ አደራ ሊሰጠው አይችልም፤ በመጀመሪያ የሆንነው ነገር፣ ተፈጥሮአዊው ገጽታችንን እና ጣዕማችንን ጨምሮ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የማይስማማ እና አብሮ የማይሄድ ነው—ኤር. 48፡11።
2. በውልደታችን የሆንነው ማንኛውም ነገር፣ መልካምም ሆነ መጥፎ፣ ጠቃሚ ሆነ አልሆነ፣ ተፈጥሮአዊ እና በአጠቃላይ መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊውን ሕይወት በማንነታችን ውስጥ እንዳያቀናብር እንቅፋት ነው፤ በዚህ ምክንያት መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ አዲስ ባህሪ፣ አዲስ ጠባይ፣ አዲስ ልማዶች፣ አዲስ በጎነት፣ አዲስ ባህሪያት መሥራት ይችል ዘንድ ተፈጥሮአዊው ብርታታችን፣ ተፈጥሮአዊው ጥበባችን፣ ተፈጥሮአዊው ጮሌነታችን፣ ተፈጥሮአዊው ባህሪያችን፣ ተፈጥሮአዊው እጥረቶቻችን፣ ተፈጥሮአዊው በጎነቶቻችን፣ ሲደመር ጠባያችንና ልማዶቻችን ሁሉ መፈራረስ አለባቸው።
3. እንደገና የማቀናበር ሥራ ለማከናወን፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በመለኮታዊው ሕይወት አብርሆት ለመስጠት፣ ለማነሳሳት፣ ለመምራት እና ለማጥለቅለቅ በውስጣችን ይንቀሳቀሳል፤ በተጨማሪም የእግዚአብሔር በኩር ልጅ የሆነውን የክርስቶስን መልክ ያስመስለን ዘንድ የተፈጥሮአዊ ማንነታችንን ገጽታዎች ሁሉ ለማፈራረስ በሁኔታችን እያንዳንዱን ዝርዝር፣ ሰው፣ ጉዳይ እና ነገር ለማዘገጃጀት በከባቢ ሁኔታችን ይሠራል—ሮሜ 8፡28-29።
4. በከባቢ ሁኔታችን ያለው ነገር ሁሉ በአምላካችን የተሰፈረልን ነው፤ ጎልቶ የሚታየውን፣ የማይረዳውን እና ጠንካራ ክፍላችንን ለመስበር ለሆነ ብቸኛ አላማ በዙሪያችን ያለውን ነገር ሁሉ ያዝዛል—መዝ. 39፡9፤ ማቴ. 10፡29-30፤ ሉቃ. 12፡6።
5. የውጪው ሰው ካልተሰበረ የውስጡ ሰው አይለቀቅም፤ የከበረው መዝገብ መለቀቅ ከመቻሉ በፊት የሸክላው ዕቃ መሰበር አለበት (2 ቆሮ. 4፡7)፤ ሽቶው በአልባስጥሮሱ ብልቃጥ ውስጥ እስካለ ድረስ መዓዛው አይለቀቅም (ዮሐ. 12፡3)።
6. ያልተሰበረ ሰው ለሌሎች መገዛት አይችልም፤ የተፈጥሮአዊው ባህሪያቸውን አመጸኛነት የሚያውቁ ክርስቶስን እንደ የመገዛት ሕይወታቸው የተለማመዱት ብቻ ናቸው—ፊልጵ. 2፡5-8።
7. ትምክህተኛ የሆነ ሰው አልተሰበረም፣ ሌሎችን የሚነቅፍ ሰው አልተሰበረም፣ ምንም ሆኖ እያለ አንዳች እንደሆነ የሚያስብ ሰው አልተሰበረም፣ ከሌሎች ጋር የሚፎካከር እርሱ አልተሰበረም—3፡3፤ 1 ቆሮ. 6፡7፤ ገላ. 5፡25-26፤ 6፡3።
8. በሌሎች ተጨቁኖ፣ ተበድሎ፣ ዝቅ ተደርጎ ወይም ተከድቶ ፈጽሞ የማያውቅ ሰው ጥሬ፣ ያልተገራ እና ለእግዚአብሔር ጥቅም-አልባ ነው፤ በእግዚአብሔር ስለተላከን፣ በእግዚአብሔር ስለተጠራን እና ሥራው አደራ ስለተሰጠን ቅዱሳን ሁሉ ያደንቁናል እና ያከብሩናል የሚል የተሳሳተ ጽንሰ-ሃሳብ ሊኖረን አይገባም፤ ዛሬ ያከበረን ነገ ሊሳለቅብን እና ከእግሩ በታች ሊረጋግጠን ይችላል፤ ጌታን የሚያገለግል ሰው መንገድ ይህ ነው።

ሐ. በተጨማሪም ከተፈጥሮአዊው ባህሪያችን ነጻ መውጣት የሚመጣው ክርስቶስ እንደ ታላቁ ብርሃን በውስጣችን ከማብራቱ ነው፤ ይህ ማብራት እግዚአብሔር የሚያየውን ማየት ነው—ምሳ. 4፡18፤ 20፡27፤ መዝ. 18፡28-29፤ ማቴ. 4፡16፤ ሉቃ. 11፡34-36፤ ሐዋ. 9፡3-5፤ 22፡6-10፤ 26፡13-19፤ ኤፌ. 5፡13፤ ፊልጵ. 2፡15-16።

1. በክርስቲያን ልምምድ ውስጥ ያለ ታላቁ ነገር ከመለኮታዊው ብርሃን ማብራት የሚመጣው መግደል ነው፤ ማብራቱ ማዳኑ ነው፣ ማየቱ ደግሞ ነጻ መውጣት ነው፤ ጌታ በክብሩ ያለውን ራእይ በእውነት ያየ ሰው ሁሉ ርኩስ ስለመሆኑ በሕሊናው አብርሆት ያገኛል—ኢሳ. 6፡1-8።

2. ጌታ እኛን ለማጋለጥና ትሁታን ለማድረግ ብዙ ብርሃን ይሰጠናል፤ እንዲህ አይነቱ ብርሃን ብቻ ትምክህታችንን ያስወግዳል፣ እንዲሁም ይህ ብርሃን ብቻ ሥጋዊ እንቅስቃሴዎቻችንን ያስቆማል፣ ውጫዊ ሽፋናችንን ከተፈጥሮአዊው ባህሪያችን ጋር ይሰብራል፤ አብዝተን እግዚአብሔርን ስናይ፣ እግዚአብሔርን ስናውቅ እና እግዚአብሔርን ስንወድ፣ አብዝተን ራሳችንን እንጸየፋለን እንዲሁም አብዝተን ራሳችንን እንክዳለን—ኢዮ. 42፡5-6፤ ማቴ. 16፡24፤ ሉቃ. 9፡23፤ 14፡26።
3. በራሳችን ጥረት በተፈጥሮአዊው ባህሪያችን ቸር ወይም ታጋሽ ለመሆን መሞከር የለብንም፤ ይልቁንም በእግዚአብሔር ብርሃን ፊት ራሳችንን ማዋረድ፣ የእርሱን መስበር መቀበል እና ከባቢ ሁኔታው እንዲሰብረንና እንዲያፈራርሰን መፍቀድ አለብን።

መ. ሰዎችን ለመንከባከብ በጌታ እጅ ጠቃሚዎች ካልሆንን፣ ምክንያቱ ተፈጥሮአዊው ባህሪያችን ነው፤ ተፈጥሮአዊ ባህሪያችንን የሚገድሉት ሦስት ነገሮች የቤተ ክርስቲያን ሕይወት፣ ፍሬ-ማፍራት እና ጠቦቶችን መመገብ ናቸው፤ ተፈጥሮአዊ ባህሪያችንን ለማስወገድ፣ እንደ ጸጋ በእርሱ ለመሰረጽ እግዚአብሔርን በመንካት እግዚአብሔርን መውደድ አለብን እንዲሁም እንደ ጸጋ እግዚአብሔርን ወደ እነርሱ ውስጥ ለማስረጽ ሰዎችን በማግኘት መውደድ አለብን—ዮሐ. 21፡15-17፤ ኤፌ. 3፡2፤ 4፡29፤ 1 ጴጥ. 4፡10።

**IV. እግዚአብሔር ያዕቆብን ማደቡ በአዲስ ኪዳን አማኞቹ ውስጥ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ቅጣት እና የመለወጥ ሥራው ሙሉ ስዕል ነው፣ ይህም ወደ ብስለት እስኪደርሱ ድረስ ክርስቶስ በእነርሱ ይሠራ ዘንድ፣ ሙሉ በሙሉ ያድግ ዘንድ ተፈጥሮአዊ ባህሪያቸውን ለማስወገድ ነው፤ ይህ በመለኮታዊው ሥላሴ መለኮታዊ እደላ ሌሎች አቅርቦት እንዲቀበሉ እግዚአብሔር እኛን መባረኩ እና እኛን ለሌሎች በረከት ማድረጉ ነው—ሮሜ 12፡2፤ 2 ቆሮ. 3፡18፤ ዕብ. 6፡1፤ ዘፍ. 12፡1-3፤ ሕዝ. 34፡26፤ ዘኁ. 6፡22-27፡-**

ሀ. የያዕቆብ ሕይወት የሚያሳየው ተፈጥሮአዊ ሰው የእግዚአብሔር ልዑል፣ እስራኤል ለመሆን በመሰበር ውስጥ ማለፍ እንዳለበት ነው፤ በከባቢ ሁኔታችን በኩል እግዚአብሔር የሚያፈራርሰው ዋጋ ቢስ የሆነውን እኔነታችንን፣ ተፈጥሮአዊ ባህሪያችንን ነው፤ ሆኖም ግን፣ እግዚአብሔር ወደ ውስጣችን የሚገነባው ነገር ወደር የሌለውን፣ እጅግ የላቀውን፣ ወሰን-አልባውን ራሱን ነው—1 ቆሮ. 3፡12።

ለ. እግዚአብሔር ያዕቆብ ዘመኑን ሁሉ የትግል ሕይወት እንዲኖር ወስኖለት ነበር፤ አታላይና ተረከዝ ያዥ የሆነውን ያዕቆብን የእግዚአብሔር ልዑል፣ እስራኤል ወደ መሆን መለወጥ ይችል ዘንድ ሉአላዊ በሆነ መልኩ በያዕቆብ ሕይወት ውስጥ እያንዳንዱን ሁኔታ እና ሰዎችን አዘገጃጀ እንዲሁም ሁሉም ነገሮች ለያዕቆብ ለበጎ እንዲሠሩ አደረገ—ዘፍ. 25፡26፤ 32፡24-32።

ሐ. የያዕቆብ በሕይወት የመብሰል (የመለወጥ የመጨረሻው ደረጃ) ጠንካራው መገለጥ ያዕቆብ ሁሉን የመባረኩ ሀቅ ነው፤ የሚያታልሉት እጆቹ የሚባርኩ እጆች ሆኑ፤ በረከት ማለት በሕይወት ብስለት በኩል እግዚአብሔር እንደ ሕይወት ወደ ሌሎች ሞልቶ መፍሰሱ ነው—47፡7፣ 10፤ 48፡14-16፤ 49፡1-28።

© 2021 Living Stream Ministry